




አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!








# ንግድና ልማት

መጋቢት 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com


## በሃላፊነት የሚከወን ቢዝነስ (RBC)፤ የጨዋ እና አስተዋይ ነጋዴ ምልክት

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በእንግሊዥኛው ምዕጻሩ (RBC) ሪስፖንሲብል ቢዝነስ ኮንዳክት በመባል የሚታወቀው ዘመናዊ የንግድ አመራር በአገራችን እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ ነገር ግን በተለያዩ መድረኮች ስለ RBC ለዘመናዊ ንግድ አመራር አስፈላጊነት ሲነሳ ይሰማል፡፡

ለመሆኑ RBC ምንድነው?፤በምን ይገለጻል? ብንልና ብንጠይቅ በተዛማጅ ትርጉሙ አንድ ነጋዴ ለራሱ እና ለሙያው ታማኝ ሆኖ ለሕሊና አድሮ እና ሕግን አክብሮ ሲሰራ እንዲህ አይነቱ ንግድ አሰራር ከሞላ ጎደል የአር. ቢሲን መርሆች የተከተለ ነው ማለት ይቻላል ይላሉ ባለሙያዎች፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል > >>

## ንግድ ም/ቤቱ በቢዝነስ ሜንተርሽፕ ለተሳተፉ አውቅና ሰጠ

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

አንጋፋ የንግድ ሰዎች ለወጣቶች ወይም ያካበቱትን ልምድ እና እውቀት ለጀማሪ ወጣት ቢዝነስ አንቀሳቃሾች የሚያካፍሉበት ዘዴዎች አንዱ የቢዝነስ ሜንተርሽፕ ነው፡፡

አንጋፋዎች ከጀማሪዎች ጋር በአካል ተገናኝተው የእርስ በእርስ ውይይት ፤የመረጃ እና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ አዲስ ቻምበር ባዘጋጀው የሜንተርሺፕ መርሃ ግብር ላይ የተሳተፉ አባላት እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል > >>

## የግንባታው ኢንዱስትሪ ፈተናዎችና እድሎች



**በአሸናፊ ምትኩ**

**"በኢትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክቶች እስከ 35 በመቶ የብረት ብክለት ይታይባቸዋል" የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል > >>




## የስኬታማ ሴቶች ጥበብና ተሞክሮ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

በቢዝነስ ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ያላቸው ፋይዳ የላቀ ቢሆንም ወደ አመራርነት ለማምጣት ግን ፈታኝ ሁኔታዎች እንዳሉ የአዲስ ቻምበር ፕሬዝዳንት ተናገሩ፡፡ ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ( ማርች 8) " ስኬታማ ስራ ፈጣሪዎች በቢዝነስ ዘርፍ አመራራ" በሚል የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ስኬታማ የቢዝነስ መሪዎችን በመጋበዝ የፓናል ውይይት መድረክ ያካሄደ ሲሆን ስኬታማ ሴቶች የቢዝነስ ልምድና ተሞክሯቸውን አካፍለዋል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል > >>


MIDROC INVESTMENT GROUP

Elfora Agro Industries P.L.C.
A Member of the MIDROC Investments Group Companies



ELFORA STANDS FOR NATURAL & QUALITY PRODUCTS !

Phone: +251-911-20-31-33, +251-911-64-40-41, +251-116-46-10-79
Fax: +251-116-45-05-03
E-Mail: elforamarketing@gmail.com
mahzeki73@gmail.com
Website: midrocinvestmentgroup.com/en

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
ካሣሁን ማሞ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
እስራኤል ማንአየ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ዮሀንስ ወ/ገብርኤል- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
መጋቢት 2015 እትም

# ርዕሰ አንቀጽ

## የዋጋ ግሽበትን መግታት የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ

የዋጋ ግሽበት ጭማሪ በየካቲት ወርም እንደቀጠለ ነው። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በየወሩ የሚያወጣው የዋጋ ግሽበት መረጃ ሁኔታ የየካቲት ወር 2015 ዓ/ም አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 34 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። የምግብ ዋጋ ግሽበት የየካቲት ወር 2015 ዓ.ም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 38.1 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

በእርግጥ የንግድ ሚዛን ጉድለት እና የዋጋ ንረት ፤ ከፍተኛ የእዳ ጫናና የውጪ ምንዛሬ እጥረት ፤የሰላም መደፍረስና ኢፍትሃዊ የንግድ ውድድር የምጣኔ ሀብቱን አንድ እርምጃ አላላውስ እንዳሉ ማየት ተችሏል።

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ጋር በተለይም በባለፉት ጥቂት አመታትም በሀገራችን የታየው ነባራዊ ሁኔታና እንድምታው ኢኮኖሚውን በተለይም የግሉ ዘርፍ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ፈጥሯል። የግሉ ዘርፍ በአገራችን ያለውን ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማስወገድ ብሎም የሁሉም ፍላጐት የሆነውን ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እውን ለማድረግ የበኩሉን እንዲወጣ ምን ይሰራ የሚለው ጉዳይ ሊታሰብበት ይገባል።

የምጣኔ ሀብት ሳይንስ ንድፈሃሳብ እንደሚያስረዳው በማደግ ላይ ባለ ሀገር ያለ የዋጋ ንረት ምጣኔ በዜሮ እና በአስር በመቶ መካከል የሚዋልል ከሆነ ጠቀሜታ አለው ። የዚህ ምክንያት ደግሞ አምራቾች ተጨማሪ ምርት እንዲያመርቱ ያነቃቃቸዋል። ሀገራዊ ምርት ይጨምራል፣ ኢንቨስትመንት ያድጋል የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመዘገብ በር ይከፍታል ። የሸቀጦችና የአገልግሎት ዋጋ መረጋጋት አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ማሳያ ነው ።

ህዝብ የሸቀጦችና የአገልግሎት የዋጋ ንረትን በእጅጉ ይጠላል። ምክንያቱም የመግዛት አቅምን በማመናመን ከዚህ በፊት ሲገዙት የነበረውን ሸቀጥ በአይነትም ይሁን በጥራት መግዛት አይቻልም።

በኢትዮጵያ የምግብ ዋጋ ወደ ላይ ከፍ እያለ መምጣቱን ከመረጃዎች ማየት ይቻላል። የምግብም ይሁን ምግብ ያልሆኑ ምርቶች ዋጋ ወደላይ እያሻቀበ የመምጣቱ ምስጢር ሊለያይ ቢችልም የፍላጎት ማደግ፣ የብር የመግዛት አቅም መዳከም፣ የአቅርቦት ማነስ፣ የገንዘብ አቅርቦት በላቀ ሁኔታ መንቀሳቀሱ፣ የብድር መስፋፋት፣ የምርቶች ከቦታ ቦታ አለመንቀሳቀስ፣ የሰላም እጦት፣የዋጋ ንረት ስጋቶች ከአለምአቀፍ የምግብ ዋጋ መጨመር ጋር የሚያያዙ ናቸውና በዚህ ዙሪያ ስራዎች መሰራት አለባቸው።

የዋጋ ንረቱ ምክንያቱ አንድና ቁርጥ ያለ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። እያደገ ያለው ስነህዝብ፣ የምርት አቅራቦት ማነስ፣ የገቢ መጨመር፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የንግድ እንቅፋቶች እና የመጓጓዣ ቅልጥፍና መድከም ለዋጋ መናር አስተዋጽኦቸው የጎላ ነው። በኢትዮጵያ ከቅርብ አመታት ወዲህ እየታየ ያለው የምግብ ዋጋ መናር በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ጤፍ፣ ሽንኩርት፣ ስንዴ፣ ቅቤ፣ የስጋ፣ ወተት ዘይት እና ስኳርን የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል።

ስለሆነም በአጠቃላይ በፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም በልዩ ልዩ ንግድ ነክ ጉዳዮች ላይ የንግዱ ህብረተሰብና መንግስት ተቀራርበው የሚወያዩባቸውን የግንኙነት መድረኮች በመፍጠር ችግሮች ስር ሳይሰዱ ቶሎ ቢቀረፉ መልካም ነው።

ስነምግባርን የተላበሰና ተወዳዳሪ የሆነ የግል ዘርፍ ለመፍጠር የግንዛቤ ስራ ለመስራት ከንግድ ምክር ቤቶች በተጨማሪ ንግድ ሚኒስቴርን የመሳሰሉ አደረጃጀቶች ቁልፉን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።
ኪራይ ሰብሳቢነትና ቅጥ ያጣ ፉክክር ለገበያውና ለተዋንያኑ አደጋ እየሆነ መጥቷል። ይህ ድርጊት በህግ ረገድ ሃይ ሊባል የሚችለው የግሉ ዘር ከሚመለከታቸው የመንግስት ባለድርሻ አካላት ጋር የማያቋርጥ ውይይት ማድረግ ሲችሉ ነው ።

በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት ለማስመዝገብ ከተፈለገ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እና የመገናኛ ብዙሀንም በኢኮኖሚያዊ አሻጥር ዙርያ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በማጋለጥ ረገድ ከምንጊዜውም በላይ መስራት ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብትም በግሉ ዘርፍ ትከሻ ይወድቅ ዘንድ በውድድር የሚያምን የፖሊሲ ማእቀፍ መንግስት መቅረጽና ወደ ስራ ማሰገባት አለበት ።

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ምቹ የንግድ ከባቢ እንዲፈጠር መንግሥት ተጨማሪ የፖሊሲ ማሻሻያ እንዲያደርግ ተጠየቀ።



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

25ኛው የአዲስ ቻምበር አለም አቀፍ የንግድ ትርዒት የመክፈቻ ሥነሥርዓት ላይ የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ባደረጉት ንግግር በአገራችን ምቹ የንግድ ከባቢ ሁኔታ እና ቀልጣፋ ንግድ ሥርዓት ለማምጣት መንግሥት የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወኑ በግሉ ዘርፍ ዘንድ በጥሩ ጎኑ የሚታይ ቢሆንም ወደሚፈለው ለመድረስ እና ሁነኛ ንግድ ከባቢ እውን እንዲሆን ተጨማሪ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በአጠቃላይ የንግድ ሥርዓቱን ለማዘመን እና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን ለመዘርጋት በመንግሥት የተከናወኑ ሥራዎች የንግዱን ሕብተሰብ ተሳትፎ ለማሳደግ ትልቅ ድርሻ አለቸው ። ነገርግን የንግዱ ሕብረትሰብ በአገራችን የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆን ተጨማሪ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ እና ቀልጣፋ አሰራሮች እንዲዘረጉ ጠይቀዋል።

በቅርቡ የተቋቋመው የካፒታል ገበያ ለንግዱ ሕብረተሰብ ተጨማሪ የፋይናንስ አማራጭ እንዲያገኝ ዕድል እንደሚሰጥ ያሰታወሱት ወ/ሮ መሰንበት ንግድ ምክር ቤቱ የነጋዴውን አንገብጋቢ የፖሊሲ እና የአሰራር ጉዳዮች እያነሳ መንግስት የፖሊሲ ማሻሻያዎች እንዲያደርግ የመወትወት ሥራውን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል ።

በክብር አንግድነት ተገኝተው ዓለማቀፉን የንግድ ትርዒት በይፋ የከፈቱት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ደኤታ አቶ እንዳለው መኮንን በበኩላቸው የወጪ ንግድ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ መንግሥት በትኩረት እየሰራ ነው ብለዋል።

የንግድ ትርዒቶች የአገራችንን ምርቶች እና አገልግሎቶች በቀላሉ ለውጪ ገበያ ለማስተዋወቅ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡ ፡ በዚህ አንጻር አዲስ ቻምበር ለረዥም አመታት መሰል የፕሮሞሽን ስራዎች በማካሄድ ሰፊ ልምድ አለው ።

መንግሥት ንግድ ም/ቤቱን አንደ አንድ ሁነኛ አጋር ተቋም አድርጎ ይመለከተዋል ብለዋል። ምክር ቤቱ የሚያካሂዳቸው ዓለማቀፍ የንግድ ትርዒቶች የአገር ውሰጥ እና የውጪ ኩባንያዎች መካከል ትስስር መፍጠር ብቻ ሳይሆን መንግሥት ቀጠናዊ እና ዓለማቀፋዊ ንግድና ኢኮኖሚያዊ ትብብር ለማጠናከር የሚያደርገውን ጥረት ጭምር አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

አዲስ ቻምበር በየዓመቱ ከሚያዘጋጀው 4 ዓለማቀፍ የንግድ ትርዒቶች አንዱ ይኸው ሁሉንም የቢዝነስ ዘርፎች የሚያሳትፈው ትርዒት ሰሆን ሌሎች 3 ዘርፍ ተኮር የሆኑ ዓለማቀፍ የንግድ ትርዒቶች ናቸው።



# በግብርና ለተሰማሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕይዞች መንግሥት ትኩረት እንዲሰጥ ተጠየቀ

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በኢንግሊዚኛው Small and Medium –Sized Enterprises (SMEs) በመባል የሚታወቁት ድርጅቶች በሌላው ዓለም ከፍተኛው የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ እና እንደ ዋና የኢኮኖሚ ሞተሮች የሚታዩ ናቸው።

ወደ አገራችን ስንመለስ የአነስተኛ እና የመካከለኛ አንቀሳቃሾች ቁጥራቸው ወደ 850 ሺጎ ይጠጋል።
ነገር ግን ቁመናቸው በአነስተኛ ቦታ፤ በአነስተኛ የሰው ኃይል እና በጥቂት ማሽኖች ወይም ሙሉ በሙሉ የሰው ጉልበት የሚንቀሰቀሱ ናቸው። የሥራ ቦታ እና ብድር ማግኘት የዘርፉ ዋነኛ ችግሮች ናቸው ።



በተለይ በግብርና የዕሴት ሰንሰለት ላይ ለተሰማሩት ኤንተርፕራይዞች በፋይናንስ አቅርቦት ላይ ያለባቸውን ችግር አስመልክቶ የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት ሰሞኑን ያስጠናው የፖሊሲ ጥናት ለባለድርሻዎች ውይይት ቀርቦ ተተችቷል።

ጥናቱ እንዳመለከተው በግብርና የዕሴት ሰንሰለቶች ላይ ለተሰማሩ አንቀሳቃሾች ብድር ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ያጋጥማቸዋል ተብሏል።

በተለይ የባንኮች የወለድ ምጣኔ እና ለብድር የማሳያዣ የሚጠይቁት ከፍተኛ የገንዘብ መጠን የብዙዎቹ ኤንተርፕራይዞች ዋና ዋና ፈተናዎች ናቸው።

በዘርፉ አንቀሳቃሾች በኩል ደግሞ ዘመናዊ የገንዘብ አያያዝ እና የአስተዳደር ክህሎት ማነስ ፤ የግብርና ቢዝነሶች ከወቅቶች እና ሳይታሰብ ከሚከሰት የአየር ፀባይ ጋር የተያያዙ መሆናቸው በባንኮች ዘንድ ለማበደር ፍራቻ መኖር ናቸው።

በጥናቱ ግኝት መሠረት ባንኮች የተለያዩ የብድር አይነቶች ያቀርባሉ። ነገር ግን በግብርና ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች የሚሰጡት ብድር ከጠቅላላው ከ2 በመቶ አይበልጥም ።

በዘርፉ ከሚንሳቀሱ ኢንተርፕራይዞች መካከል በማዳበሪያ ፤በምርጥ ዘር እና በግብርና ግብአት አቅራቢዎች፤የእርሻ እና የእንስሳት ውጤቶች አቀናባሪዎች ይገኙበታል። ስለዚህ በዘርፉ የሚታየውን የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ መንግሥት ያስቀመጠውን ዝቅተኛ የወለድ ምጣኔ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማሻሻያ እንዲያደርግ ምክረሃሳብ ቀርቧል።

በእንቅስቃሴ ላይ ላሉ ኢንተርፕራይዞችን መደገፍ፤የዘመናዊ የዲጂታል ብድር አገልግሎቶቸን ማስፋፋት ያስፈልጋል የሚሉት ምክረ ሃሳቦች በጥናቱ ቀርበዋል።

መንግሥት በገጠሩ አካባቢ ዘርፉ የሚጠይቀውን መሠረተ ልማት ጎን ለጎን እንዲዘረጋ እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ ጋር በትብብር መርጎ መሥራት አለበት ተብሏል።

የኡጋንዳ፤የማሌዢያ እና የጋናን ተሞክሮዎችን የዳሰሰው ይኸው ጥናት በገጠር አካባቢ ያሉ አንቀሳቃሾች የእርሻ መሬታቸውን አስይዘው ብድር እንዲያገኙ የሚፈቅድ አሰራር መንግሥት እንዲዘረጋ ጥናቱ የፖሊሲ ምክረሃሳብ ሰንዝሯል።

ንግድ ምክር ቤቱ ከአውሮጳ ሕብረት ጋር በትብብር ባዘጋጀው ውይይት ላይ ለጥናቱ ማዳበርያ የሚሆኑ በርካታ አስተያየቶች እና ሃሳቦች ከተሳታፊዎች ተሰንዝረዋል።

# የአዲስ ቻምበር የቢዝነስ ማበልጸጊያ/ ኢንኩቤሽን/ ማዕከል ለስራ ፈጣዎች የሚሰጠውን ስልጠና ጀመረ!!!



**በከፍያለው ዋሲሁን**

በስራ አጥነት ምክንያት ሊመጣ የሚችልን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት ለመታደግ የበኩሉን እየሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ አስታወቀ።
ይህንን ያሉት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተ ማርያም የአዲስ ቻምበር የቢዝነስ ኢንኩቤሽን/ የቢዝነስ ማበልጸጊያ/ ማዕከል ለስራ ፈጣዎች ያዘጋጀውን ሰልጠና በከፍተቱበት ወቅት ነው ።

በኢትዮጵያ እድሚያቸው ከ19 እስከ 25 የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸው እድልም ፈተናም ነው ያሉት አቶ ሺበሺ ወጣቱ ስራ እንዲፈጥር ልንደግፈው ይገባል ብለዋል።

በየአመቱ ከመንግስትና ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ተመርቀው እንደሚወጡ ጠቁመው ወጣቱ ስራ እንዲፈጠር እና ወደ ቢዝነስ እንዲገባ ልንደግፈው ይገባል ብለዋል ።

ይህንን በማድረግ በስራ አጥነት ምክንያት ሊመጣ የሚችልን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፈተና እንደንግድ ምክር ቤት ልንታደገው እንችላለለን ያሉት አቶ ሺበሺ ፤ አዲስ ቻምበር ከአውሮፓ ህብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት የቢዝነስ ኢንኩቤሽን ማዕከል አቋቁሞ ስራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ እየሰራ ይገኛል ብለዋል ።

የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከሉ የፕሮጀክት ስራ አሰኪያጅ አቶ አማኑኤል ለማ በበኩላቸው ማዕከሉ በዋናነት ወጣት እና ጀማሪ የስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰው እንዲህ አይነት ፕሮጀክቶች ሀገርን የመለወጥ አቅም አላቸው ብለዋል።

አቶ አማኑኤል አክሎም 90 በመቶ የሚሆኑት ስራ ፈጣሪዎች አምስት አመት ሳይሆናቸው የሚከስሙ መሆናቸውን ገልጸው ፤ ይህ የሚሆነው ወድቆ የመነሳት ልምድ ባለመኖሩ ነው ብለዋል።

የቢዝነሰ ማበልጸጊያ ማዕከሉ ስራ ፈጣሪዎች ለመደገፍ ሰልጠናዎችን ጀማሪ እና በስራ ላይ ላሉ በሚል በሁለት ከፍሎ እንደሚሰጥ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ ገልፀዋል ።

ለጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች የክህሎት ስልጠና ከመሰጠት ባሻገር የስራ ማሰጀመሪያ ገንዘብ ወይም seed money የሚያገኙ ሲሆን ፤ በዚህም በመጀመሪያ ዙር ከ 10 ድርጅቶች ለተውጣጡ 20 ስራ ፈጣሪዎች ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል።

ስራ ላይ ላሉና የቢዝነስ ሃሳብ ድጋፍ ለሚፈልጉ ደግሞ ሰልጠናው እስከ አራት ወራት ድረስ የሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው አብዛኛው ስራ በተግባር ስራ ላይ ሆነው የሚሰጣቸው መሆኑን ሰምተናል። ።

ቢክ ኢትዮጵያ አዲስ ቻምበር ከአውሮፓ ህብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የተቋቋመ ፕሮጀክት ሲሆን ለአራት አመት ለስራ ፈጣሪዎች ድጋፍ የሚያደርግ ፕሮጀክት መሆኑን በፕሮግራሙ ላይ ተገልጿል ።

# በኢትዮጵያ የቼክ ሪፐብሊክ አምባሳደር ከአዲስ ቻምበር አመራሮች ጋር የሁለቱ አገራት ንግድን ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መከሩ ።

**በከፍያለው ዋሲሁን**

በኢትዮጲያ የቼክ አምባሳደር ሚሮሰላቭ ኮሴክ ከአዲስ ቻምበር የቦርድ ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤና ፣ ከዋና ፀሀፊው አቶ ሺበሺ ቤተማርያም ጋር በምክር ቤቱ የቦርድ መሰብሰቢያ አዳረሽ የሁለቱ አገራት ነጋዴዎች ተጠቃሚ መሆን በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል ።

የሁለቱ አገራት ግንኙነት ረጅም ዘመን ያስቆጠረ መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደር ሚሮሰላቭ ኮሳክ ፤ ቼክ ሪፐብሊክ ከኢትየጵያ ጋር በንግድና እና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በባህል መልካም የሚባል ግንኙነት አላት ብለዋል ።

የቼክ ኩባንያዎች በጤናው ዘርፍ ፣ በግብርና ፣ በምግብ ማቀነባበር ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ መዋለ ንዋያቸውን በኢትዮጵያ ማፍሰሳቸውን አንስተዋል ።

አክለውም ሀገራቸው ቡና ፣ እና አበባ የመሳሰሉ የግብርና ምርቶችን እንደምታስገባ ጠቅሰው ፤ በተለይ ቡና ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ ተናግረዋል ።

የአዲስ ቻምበር ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው ኢትዮጰያና ቼክ ሪፐብሊክ ጠንካራ የሚባል ግንኙኘነት እንዳላቸው ጠቅሰው በኮቪድ ምክንያት ተቀዛቅዞ የነበረውን የንግድ ግንኙነት ቀድሞ ወደነበረበት ለመመለስ ኤምባሲው እያደረገ ያለውን ጥረት አድንቀዋል ።

አዲስ ቻምበርም የንግድ ግንኙነቱ ዳግም ወደ ነበረበት ለመመለስ እንደሚሰራ አረጋግጠዋል ።

የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው ባለፉት ዘመነ መንግስታት ቼክ በመከላከለያ ዘርፍ ፣ በህክምና ፣ በምግብ ማቀነባበር፣ በድልድይና መሰል የግንባታ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ አስተዋፆ ነበራት ብለዋል።

በአውሮፓዊያኑ ከ2013 እስከ 2018 ድረስ በነበረ ፕሮጀክት አማካኝነት ጠንካራ ግንኙነት በመመሰረት ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና ከኢትዮጵያ እንድትገዛ መደረጉን ገልፀዋል ።

የቼክ ኩባንያዎች በተመረጡ ዘርፎች ማለትም በማዕድን ፣ በአውቶሞቲቪ ኢንዱስትሪው ፣ በግብርናው እና በቢራ መጠጥ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራቸው ብለዋል ።

በቼክ ኢምባሲ የንግድ አታሼው ፓቬል ሳር በበኩላቸው ግንኙነቱን ቀድሞ ወደነበረበት ለመመለስ የቼክ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር መስሪያ ቤት የቼክ-አፍሪካ የንግድ ጉባኤ የፊታችን ሚያዚያ እንደሚካሄድ አስታውቀዋል ።

በአውሮፓዊያኑ ከሚያዚያ 26 - 27 /2023 በሚካሄደው ጉባኤ ላይ የአፍሪካ አገራት ንግድ ምክር ቤቶች አሁናዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና የንግድ እድሎችን የሚያስተዋውቁበት መድረክ ነው ብለዋል ።

በተጨማሪም ነጋዴዎች በተለያዩ ዘርፎች ከተሰማሩ የቼክ ኩባንያዎች ጋር ተገናኝተው በጋራ ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ የሚያመቻቹበት የንግድ ለንግድ ውይይትም ይካሄዳል ብለዋል።

ይህም ለኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች አዳዲስ አጋሮችን ለማግኝት መልካም እድል የሚፈጥር በመሆኑ ንግድ ምክር ቤቱ እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል ።


አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER
14TH ADDIS CHAMBER INTERNATIONAL
AGRICULTURE & FOOD TRADE FAIR
14ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የእርሻና ምግብ ንግድ ትርዒት
May 11-15, 2023 (ከግንቦት 3 እስከ 7 ቀን 2015 ዓ.ም.)
14TH
AGRIFEX ETHIOPIA
"Maximizing Value Additions through Agro Business"
Food processing


አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER
2ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የሜዲካል እና ፋርማሲዩቲካል ንግድ ትርዒት
THE 2ND ADDIS CHAMBER INTERNATIONAL
MEDICAL & PHARMACIUTICAL TRADE FAIR
May 11-15, 2023 (ከግንቦት 3 እስከ 7 ቀን 2015 ዓ.ም.)
ይቻላል
It's Possible!
PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP
FOR ENHANCED MEDICAL SERVICES

# በሃላፊነት የሚከወን ቢዝነስ (RBC)፤ የጨዋ እና አስተዋይ ነጋዴ ምልክት...

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**




...የአር.ቢሲ. መርሆች የሚመነጩት አገራችን የፈረመችው ዓለማቀፍ እና የአገር ውስጥ ሕግጋት፤የህብረተሰቡ ባሕል እና የሞራል እሳቤ እንዲሁም በጎ ሕሊና ናቸው ተብለው ይመደባሉ።
አንድ ቢዝነስ ሲቋቋም ነግዶ የማትረፍ ዓላማ ይዞ ነው የሚቋቋመው።ይህንን ዓላማ ሲያሳካ በዘላቂነት ደግሞ ቢዝነሱ የሚፈልጋቸው፤ወይም ሕብረተሰቡ የሚፈልጋቸው መሠረታዊ ፍላጎት ከሥራው ሂደት ጋር እያጣጣመ እንዲሄድ የሚያሳይ ነው።

የRBC መሠረታዊ ዕሳቤው አንድ የንግድ ድርጅት የንግድ አንቅስቃሴውን በሚያከናውንበት ወቅት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሰውን እና አካባቢን ከሚጎዱ ማንኛውም ያልተገቡ ድርጊቶች አንዲታቀብ የሚያሳስብ የንግድ ሥነምግባር መመሪያ ነው ማለት ይቻላል ።

የቢዝነስ ድርጅቶች ከተቀጣሪ ሠራተኞች መብት አንስቶ እስከ አካባቢ እንክብካቤ ሕግጋትን አክብረው አንዲንቀሳቀሱ የሚጠይቀው ዓለማቀፍ መርህ በአገራችን ብዙም የተለመደ አይደለም።
በዓለም ገበያ ላይ እንደ ውድድር መስፈርት እየሆነ የመጣውን ዘመናዊ የንግድ መርህ በአባላቱ ዘንድ ግንዛቤ ለመፍጠር የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት በቅርቡ አንድ ሥልጠና አዘጋጅቶ ነበር።
ሥልጠናው ከፓፓያ የዕሴት ሰንሰለት ጋር ግንኙነት ያላቸው ኩባንያዎችን ያሳተፈ ሲሆን የRBC መርሆችን እንደ ድርጅታቸው ጸባይ አስማምተው መተግበር አንዲችሉ ያመላከተ ነበር።

### “ከተባባሪዎቻቹ ጋር ያለንን ትስስር ጤነኛ የሚያደርግ እና በቡድን መሥራትን የሚያዳብር ነው”



**አሳምነው አብዩ(ዶ/ር) -ከቫይታል አርት ኩባንያ**

የአር ቢ.ሲ ስልጠና እውነት ለመናገር ጥሩና ወቅታዊ የሚባል ነው። እኔ የአዲስ ቻምበር አባል ከሆንኩኝ 4አመቴ ነው። ስልጠናው ስለ ንግድ ስነምግባር / ኢንቴግሪቴ/ በተለይ ኃላፊነትን በጠበቀ መልኩ የቢዝነስ ግንኙነት እንድናደርግ የሚረዳ ነው።
ቀጥረን ከምናሰራቸው ሠራተኞች ጋር ብሎም አብረን ከምንሠራቸው ተባባሪዎች ጋር ያለንን ትስስር ጤነኛ የሚያደርግ ፤በቡድን መሥራትን የሚያዳብር ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ወድጄዋለሁ ብዙ ተጠቅሜበታለሁ።

### “RBC አንድ ድርጅት በውስጡ ምን እየሰራ ነው የሚለውን ለማወቅ ይረዳል”



**ይታገሱ ታደሰ (ከፋፋ ምግብ አ.ማ)**

አቶ ይታገሱ ይህ ጉዳይ በድርጅታቸው በቀጥታ በሥራ ላይ ባይውልም የዓለማቀፉ ደረጃዎች ድርጅት (ISO) የሚጠይቀውን RBC አንድ ድርጅት በውስጡ ምን እየሰራ ነው የሚለውን ለማወቅ ይረዳል ይላሉ ። ስልጠናው ለሠራተኛው ምን ያህል ድጋፍ ያደርጋል፤ከሴፍቲ አንጻር..ለእኛ ድርጅት ከውጪ በኩል ያለንን ግንኙነት እና ምርታችን በሕ/ሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው ወይ የሚለውን ለማወቅ ይረዳል።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል > >>

# የስኬታማ ሴቶች ጥበብና ተሞክሮ



በፓናል ውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የንግድ ምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ሴቶች ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዳይመጡ የቤት ውስጥ ጫና መብዛት ከሚያጋጥሙዋቸው ተግዳሮቶች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰው ይህን ለመለወጥ መስራት እንደሚያስፈልግ ምክረሀሳባቸውን ለግሰዋል።
የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ፀሀፊ ወ/ሮ መብራት ነማርያም በበኩላቸው አዲስ ቻምበር ሴቶችና ወጣቶች ስራ ፈጥረው በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።
ሴቶች በኢኮኖሚ ውስጥ ንቁ ሚና እንዲጫወቱ ፤የስራ ፈጠራ ክህሎታቸው እንዲዳብር እና የንግድ ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።
በፓናሉ ልምድና ተሞክሯቸውን ያካፈሉት የካሊድስ ቡና መስራችና ባለቤት ወ/ሮ ፀደይ አስራት ሴቶች በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ቢኖሩባቸውም ያንን ማለፍ እንደሚቻል የእርሳቸውን ተሞክሮ በምሳሌነት አቅርበዋል።
ከቤት ውስጥ ኃላፊነት ጀምሮ ካፍቴሪያዎችን እስከማስተዳደር ያሉ ድርብርብ ኃላፊነት እንዳሉባቸው የመሰከሩት ወ/ሮ ፀደይ ድርጅታቸውን ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ 40 ማሳደጋቸው ትልቅ ስኬት እንደሆነ ተናግረዋል።
በተለይ ሴቶችን ወደ ኃላ ሊያሰቀሩ የሚችሉ በርካታ እንቅፋቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የተናገሩት እኚህ ስኬታማ የቢዝነስ ሰው ጩሆቶችን ሳያዳምጡ መስራት ውጤታማ እንዳደረጋቸው ገልፀዋል።
ስኬታማ እንደሚሆኑ ያውቁት እንደነበር የገለፁት ወ/ሮ ጸደይ በበኩላቸው ፈተናዎችን ለመወጣት የሄዱበት መንገድ የሰኬት ምንጮች መሆናቸውን ተናግረዋል ።
የሚክራ ሞተርስ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መስራችና ስራ አስኪያጅ የሆኑት ወ/ሮ ኢክራም ኢድሪስ የጋራዥ ስራ ለወንዶች ብቻ የተተወ ሙያ ተደርጎ የሚታይ መሆኑን ጠቁመው ፤ ፈተና ቢኖረውም ፈተናውን ተቋቁመው እየሰሩበት እንደሚገኙ ተናግረዋል።
ስኬት በተንደላቀቀ ቪላ ቤት መኖር አሊያም ዘመናዊ መኪና መንዳት አይደለም ያሉት ወ/ሮ ሚክራ ሴቶችን እንዲሰሩ በመደገፍ አገር እንዲቀይሩ ማድረግ ሲቻል ነው ስኬታማ የምሆነው ሲሉ ስኬት ምን ማለት ነው ለሚለው ጥያቄ ምላሻቸውን የሰጡት ።
ሴቶች ከስራ በተጨማሪ በቤት ውስጥ ተደራራቢ ኃላፊነት የተጣለባቸው መሆኑን የጠቀሱት የውዳሴ ግሩፕ ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ውዳሴ እንቁ ብርሃን ሀላፊነትን በማከፋፈል ( ስራን ሴቶችን ወደ ቢዝነስ አመራር እንደሚመጡ ማድረግ አለብን ብለዋል ።
እኚህ የቢዝነስ ሰው ምንም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል የፈጠረ ኩባንያ እየመሩ ቢሆንም ስኬት ላይ ለመድረስ ገና መሆናቸውን ተናግረዋል።
በመጨረሻም የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ንግድ ምክር ቤታቸው በንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሴቶች የበኩሉን ድጋፍ ማድረጉን እንደሚቀጥል ተናግረዋል ።

# የ25ኛው አዲስ ቻምበር ዓለማቀፍ ንግድ ትርዒት ትሩፋት

**(በይድነቃቸው ዓለማየሁ)**



**... ከአዳማ ላይ አንድ የምግብ ዘይት ፋብሪካ ለማቋቋም ዕቅድ አለን**
(ቻንድራ ጉፕታ ፤ ጉዮ ግሩፕ፤ ከሕንድ)

እኛ የተሰማራነው በምግብ ዘይት ማምረት ዘርፍ ላይ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ጉዮ ግሩፕ የእንስሳት መኖ አና በቆሻሻ አወጋገድ ቴክኖሎጂ ሥራዎችንም ላይ ተሰማርተናል፡፡
በኢትዮጵያ ከ100 ሚሊየን ሕዝብ በላይ ይኖራል፡፡ ይሄ ቁጥር ለኛ ትልቅ ገበያ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ አዳማ ላይ አንድ የምግብ ዘይት ፋብሪካ ለማቋቋም ዕቅድ አለን ፡፡
እግረ መንገዳችን ኢትዮጳያ በውጪ ምንዛሬ የምታስገባውን የምግብ ዘይት በአገር ውስጥ አምርተን ለመተካት ጥረት እናደርጋለን፡፡ ዝግጅቱ መልካም ነው... በአዲስ ቻምበር የንግድ ትሪዒቶች ስንሳተፍ ቆይተናል፡፡
ዛሬም ቻምበሩ ባመቻቸልን ዕድል ጥሩ ጥሩ ደንበኞችን አግኝተናል፡፡ ምርት እና አገልግሎታችንን ለብዙ ጎብኚዎች እያስተዋወቅን ነው፡፡
ከአዳዲሶቹ ደንበኞቻችን ጋር ጥሩ የቢዝነስ ግንኙነት እንጀምራለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን ፡፡



**ከበርካታ ደንበኞች ጋር ተገናኝተናል**
መሐመድ ቻባሪ (ከቴክኖ ኮያል)

እኛ በትርዒቱ ላይ ይዘን የቀረብነው የሞተር ዘይቶች እና ቅባቶችን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የተሽከርካሪዎች፣ የኢንዱስትሪዎች ፤ ማሽኖች ቁጥር እያደገ ነው፡፡ ለእነዚህ የሚሆኑ ዘይቶች እና ማለስለሽ ቅባቶች እናቀርባለን፡፡ በኢትዮጵያ ሰፊ ገበያ እንዳለ አውቀናል፡፡ ስለዚህ በቀጣይ ገበያችንን ለማስፋት እንፈልጋለን፡፡ በርካታ ደንበኞች ጋር ተገናኝተናል፡፡ እስከ አሁን ያለው ነገር ጥሩ ነው፡፡



**...ከአገራችን ሳንወጣ እና ተጨማሪ ገንዘብ ሳናወጣ ከዓለም ዙሪያ ከሚመጡ ደንበኞች ጋር መገናኘት ችለናል፡፡**
ምክሩ ዳንቢ (ከለዊታ ኃ.የተ.የግ,ማሕ)

ኩባንያችን የቡና፤የቅባት እና የጥራጥሬ እህሎችን ለውጪ ገበያ ያቀርባል፡፡ የግብርና ግብዓቶችንም ለአገር ውስጥ ገበያ እናቀርባለን፡፡
በዚህ አግዚቢሽን ላይ በመሳተፋችን ደስተኞች ነን፡፡ እዚሁ ከአገራችን ሳንወጣ ፤ሳንጓዝ እና ተጨማሪ ገንዘብ ሳናወጣ ከዓለም ዙሪያ ከሚመጡ ደንበኞች ጋር መገናኘት ችለናል፡፡
የንግድ ትርዒቱ ደንበኞቻችን እዚሁ መጥተው ምርታችንን በአካል ተገኝተው ፤ በዐይናቸው ተመልክተው በቀላሉ መተማመን ላይ ደርሰን የቢዝነስ ውለታዎች እንድናስር ይረዳናል ብዬ አስባለሁ፡፡
ደንበኞቻችን ከዚህ ተገኙ ማለት የምናቀርብላቸውን ምርቶች በናሙና ደረጃ ሳይሆን የምንልክላቸው ምርቶች አስተማማኝነት እና ጥራቱን ካለበት ቦታ ላይ እንድናሳያቸው ያስችለናል፡፡ ስለዚህ የአዲስ ቻምበር ንግድ ትርዒቶች ለእኛ ትልቅ ጥቅም አላቸው፡፡
የውጪ ንግድን ለማሳደግ መንግሥት ቁርጠኝነቱን ሰምተናል፡፡ በእኛ በኩል ደግሞ የምንልከውን ምርት ጥራቱን ጠብቀን ፤በገባነው ውል መሰረት ሳናጎድል ለውጪ ተቀባዩቻችን በታማኝነት መላክ አለብን፡፡ የአገራችን ላኪዎች ቃላችንን ጠብቀን በተስማማነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርታችንን ከቦታው ማድረስ አለብን፡፡ ምክንያቱም በውጪ ያሉ ደንበኞቻችን ምርታችንን የሚገዙት የዓለም ገበያን አስቀድመው ገምተው ነው፡፡ ለደንበኞቻችን በጊዜ ካላቀረብን ገበያችንን በሌሎች እንነጠቃለን፡፡ ስዚህ ኤክስፖርታችንን ለማሳደግ ላኪዎች ጠንክረን መሥራት አለብን፡፡



ቴዎድሮስ (ከጃቢ ንግድና ኢንዱስትሪ)

ኩባንያችን በኤክስፖርት እና ኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ንግድ ላይ ይሰራል፡፡ ንግድ ትርዒቱ ዓለማቀፍ መድረክ ስለሆነ ትልቅ ዕድል አግኝተናል፡፡ በዛው ልክ የማናውቀውን አዳዲስ ማሽነሪዎች ለማየት ችላናል፤ ጥሩ የልምድ ልውውጥ አድርገናል፡፡ መድረኩ ሰፊ ስለሆነ ለእኛ በጣም ይረዳናል ማለት እችላለሁ፡፡



ያኪል ሐሰን (ከአሰዶድ ኩባንያ - ሱዳን)

እኛ ለተቀነባበሩ ምግቦች የሚሆኑ የተለያዩ ማሽጊያዎችን እናመርታለን፡፡ ዛሬ ከእዚህ የተገኘነው አዲሱን የማሽጊያ ምርታችንን ለማስተዋወቅ ነው፡ ፡ አዲሱ ማሽጊያ ለወተት እና ለወተት ተዋጶኦዎች በጠቅላላ እናመርታለን፡፡
በተለይ የዐይብ ማሽጊያዎቻችን በከፍተኛ ጥራት እናመርታለን፡፡ እኛ ይዘን የቀረብነው የታሸገ ዐይብ በቀላሉ ሰዎች ገዝተው በፈለጉት ቦታ እና ጊዜ እዲመገቡት ነው፡፡ ለቤተሰብ እና ለነፍስ ወከፍ ፍጆታ እንዲመች አድርገን በተለያዩ ግራሞች አዘጋጅተን ጥራት ያለው የዐይብ ምርት እናቀርባለን፡፡
አሁን እዚህ ንግድ ትርዒት ላይ በኢትዮጲያ ወኪሎች አግኝተን በጋራ ለመሥራት እንፈልጋለን፡፡ ገበያችንን ወደ ሌሎች የአፍሪቃ አገራት ለማስፋት ዕቅድ አለን፡፡ በዚህ መሠረት አሁን ከኢትዮጵያ ጀምረናል፡፡

# ንግድ ም/ቤቱ በቢዝነስ ሜንተርሽፕ ለተሳተፉ አውቅና ሰጠ...

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

ንግድ ም/ቤቱ በየዘርፉ ከመደበላቸው አንጋፋ የንግድ ሰዎች ጋር በሚመቻቸው ጊዜ እና ቦታ እየተገናኙ ምክክር እንዳደረጉ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ተናግረዋል፡፡
በንግድ ምክር ቤቱ ከተሰየሙት ሜንተሮች መካከል አንዱ አቶ ሐሰን የሱፍ የተባሉ የአምባሰል ትሬዲንግ ሃውስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆኑ የተመደቡላቸውን በኤክስፖርት ዘርፍ ለተሰማሩ ወጣት ላኪዎችን መረጃ እና ምክር በመስጠት ፤ በስነልቦና በማዘጋጀት እንዲሁም በውጪ አገር ከሚገኙ ደንበኞች ጋር እንዲገናኙ እና ሥራ እንዲጀምሩ ድጋፍ ማድረጋቸው ተወስቷል፡፡
አዲስ ቻምበር የአባላቱን በዓለም ገበያ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፡፡



ይኸው የሜንተርሽፕ መርሃግብር ከአቅም ግንባታ ሥራዎች አንዱ መሆኑን የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ዘካሪያስ አሰፋ ለተሳታፊዎች የምክር ወረቀት ከሰጡ በኋላ ተናግረዋል፡፡
ሰልጣኞች በበኩላቸው በሜንተርሺፕ መርሃግብሩ ስለንግድ ሥራ አመራር ሰፊ እውቀቶችን እና ልምዶችን ለመቅሰም መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡
በውጪው ዓለም የሜንተርሺፕ አገልግሎት ገንዘብ ተከፍሎበት እና በቀጠሮ የሚሰጥ ሙያዊ አገልግሎት ነው፡፡ ነገር ግን የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት በጎ ፈቃደኛ የንግዱን ሕብረተሰብ አባላት በማስተባበር ለጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች አገልግሎቱን በነጻ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን እንዳመቻቸ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# “መንግስት የግሉ ዘርፍ በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ ...



ቢሆን የሚመነጨው ከእያንዳንዱ ዜጋና መንግስት እንደሆነ ይታመናል። በዚህ መጣጥፍ የግሉ ዘርፍ ለሰላም መስፈን የሚኖረው ሚና ምን መሆን እንዳለበት የምናስነብባችሁ ይሆናል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አሁን ላይ የግሉ ዘርፍ ለኢኮኖሚም ሆነ ለፖቲካዊ መረጋጋት የሚጫወተው ሚና ወሳኝ እንደሆነ ያምናል። አለም በአራቱም አቅጣጫ ውጥረት ውስጥ በገባችበት በዚህ በያዝነው ክፍለ ዘመን የግሉ ዘርፍ የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ በማረጋጋት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያምናል። መንግስታት ሰላም እንዲሰፍን ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን የንግዱ ማህበረሰብ ሚናም ከፍተኛ እንደሆነ እሙን ነው። በተለይም ንግድን በቅንነትና በታማኝነት መስራት በራሱ ኢኮኖሚ እንዲያድግ የስራ እድል እንዲፈጠር ብሎም የተረጋጋ የንግድ ሂደት እንዲሰፍን በማድረግ በተዘዋዋሪ ሰላማዊ የሆነ ማህበረሰብ ወይም ሀገር እንዲኖር ያስችላል በማለት አቶ ኤልያስ ገነቲ የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የቀድሞ ፕረዚደንት ተናግረዋል። አንዱ የፖለቲካ መረጋጋት ሊመጣ የሚችለው ወይም የሰላም ችግር የሚፈታው ድህነትን ሊቀንስ የሚችል የቢዝነስ ማህበረሰብን መፍጠር ሲቻል ነው ብለዋል አቶ ኤልያስ ገነቲ። በተለይም መንግስት የግሉ ዘርፍ በሀገሩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ንቁ ሚና እንዲኖረው በማድረግ ድህነትና ስራ አጥነት እንዲቀንስ በማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተረጋጋ ሀገር እንዲኖር ማድረግ ይችላል ብለዋል አቶ ኤልያስ ገነቲ። የግሉ ዘርፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባዋል ያሉት አቶ ኤልያስ ይህን ማድረግ ከተሳነው ግን በሰላም መደፍረስ ዋና ተጎጂ የግሉ ዘርፍ ነው ብለዋል። በሰሜን ኢትዮጵያ በተቀሰቀሰው ጦርነት የእርሻ ኢንቨስትመንት እንደወደመባቸው የተናገሩት አቶ ኤልያስ ጉዳቱ ለባለሀብቱ ብቻ ሳይሆን ለገበሬ ፣ለነጋዴው፣ ለማህበረሰቡ እና ሀገርን የውጭ ምንዛሬ ያሳጣል ብለዋል። በመሆኑም እንዲህ አይነት ውድመቶችን ለማስቀረት የሚያስችል የሰላም ግንባታ መማክርት ጉባኤ መፍጠር ያስፈልጋል በማለት ምክረሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንዲህ አይነት አወቃቀሮችን በስፋት በማስፋፋት የሰላም አስፈላጊነት ላይ ሰፊ ስራን መስራት ያስፈልጋል ብለዋል። በመንግስት ተነሳሽነት የተፈጠረው ብሄራዊ የምክክር መድረክ በኢትዮጵያ ቅራኔዎች እንዲፈቱ እና አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ እንዲሰፍን ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል ያሉት ደግሞ አስማ ረዲ ከሰላም ሚኒስቴር ናቸው። የግሉ ዘርፍ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ሰራተኞች በሰላም ዙርያ በማወያየት የሚኖረው ሚና ትልቅ በመሆኑ ይህን ታሳቢ ያደረገ ስራ መሰራት አለበት በማለት ምክረሀሳባቸውን አካፍለዋል። የንግዱ ማህበረሰብ የሰላም መማክርት ጉባኤ ሊመክርበት የሚችልበትን መድረክ መፍጠር ተቃማቸው ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል አስሊ ረዲ። ንግድ ለሰላም በሚል ርእስ በቅርቡ በኢኒሽየቲቭ አፍሪቃና በአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በጋራ ባዘጋጁት የምክክር መድረክ ላይ የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች በሰላም ዙርያ ለመንግስት በተለይም ለሰላም ሚኒስቴር በርካታ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ እንዲሰፍን በመድረኩ ላይ ጥሪ አቅርበዋል። ከነዚህ ሀሳቦች መካከል በኢትዮጵያ እየተባባሰ የመጣውን የሰላም እጦት የሰላም ሚኒስቴር ለመፍታት የወሰደው እርምጃ በተጨባጭ ችግሮቹን በሚፈለገው ልክ መፍታት አለመቻላቸውን፤በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ የሰላም ሚኒስቴር የንግዱን ማህበረሰብ ለማሳተፍ ያደረገው ጥረት አናሳ መሆን፤መንግስት አስተማማኝ ሰላምን በማስፈን የንግዱ ህብረተሰብ በተረጋጋ ሁኔታ የንግድ ስራውን እንዲያከናውን ማድረግ አለበት፤ የሰላም ግንባታ ተቋማት በተጨባጭ ሰላምን ለማስፈን የሚያደርጉት ጥረት ማደግ አለበት፤ የሚወጡ ፖሊሲዎች የንግዱን ማህበረሰብ በሰላምና ሀገር ግንባታ ቀጥተኛ ተሳታፊ ማድረግ አለባቸው የሚሉ ሀሳቦች ተነስተዋል። ከዚህም ባለፈ የሰላም ሚኒስትር ዜጎች በሀገር ግንባታ ያላቸው ተሳትፎ እንዲያድግ ሰፊ ስራ መስራት አለበት የሚሉ አስተያየቶችና የንግዱ ማህበረሰብ ከዘረኝነት እና ከፋፋይ ሃሳቦችን በመካላከል የራሱን ሚና መጫወት እንዳለበት ፤የሰላም ሚኒስትር አወቃቀሮች እስከ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ ማውረድ እና መተግበር አለባቸው የሚሉ አስተያየቶች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለበርካታ አመታት የተዘራውን የዘረኝነት መርዝን በመዋጋት ተሻለች ሀገር እና ኢኮኖሚን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ሀሳቦች ቀርበዋል። መንግስት እና የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት የንግዱ ማህበረሰብ የሚያቀርባቸውን ምክረሃሳቦች እና አስተያቶችን በማስተናገድ በቀጣይ ለሚወሰዱ ፖሊሲ ነክ እርምጃዎች እንደ ግብአት ይጠቀምባቸው ዘንድ እንጠቁማለን። ምክንያቱም የአንድ ሀገር ሰላምና ጸጥታ ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት በማገዝም ሆነ ጽኑ ማህበረሰብን ከመፍጠር አኳያ ያላቸው ሚና አይተኬ በመሆኑም ጭምር ነው።

**ሰላም ለሀገራችን!**



## ከአድቮከሲ ጓዳችን…

# ሥጋት እና ተስፋ በባንኮች መንደር…

**…አገር በቀል ባንኮቹ ቁጭ ብለን በጋራ ማሰብ ፤መወያየት፤ነገሮቹን በጥንቃቄ ማየት አለብን**

**አቶ አስፋው ዓለሙ፤ የዳሽን ባንክ ፕሬዝደንት**



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በእኔ እይታ የውጪ ባንኮች ለመግባት ትልቅ ፍላጎት አላቸው። በተለይ በአካባቢው አገራት የሚንቀሳቀሱት በጣም ለመግባት ይፈልጋሉ። ለምን ፈለጉ ቢባል ያው ትርፍ ለማግኘት ነው። ወደ እኛ አገር በሚመጡበት ጊዜ አትርፈው ለመውጣት ይፈልጋሉ። ስለዚህ ትርፍ በሚገኝበት የባንክ አገልግሎቶች ላይ በሰፊው ይሰማራሉ ብዬ እገምታለሁ። ባንኮች አንዳንዴ እስከ 75 በመቶ ድረስ የትርፋቸው ምንጭ ብድር ሰጥተው የሚያገኙት ወለድ ነው።

በግላቸው እራሳቸውን ችለው ቢገቡም ወይም ከሌላ ባንክ ጋር በጥምር ቢገቡም የብድር አይነቶችን አስፍተው ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

2ኛ የሚጠበቅ ጉዳይ ቢኖር አሁን አሁን ትልቁ የባንኮች የገቢያቸው ምንጭ የሆነው ትሬድ/ የንግድ ፋይናንሱ ነው። የወጪ እና የገቢ ንግዱ ላይ የሚሰሩት ሥራ ነው። በዚህ ዘርፍ ላይ ትልቅ ፍላጎት አላቸው። ሰለዚህ በውጪ ምንዛሬ ፍሰት አንደ አማራጭ ባንክ ሆነው ጥሩ አስተዋጽኦ ይደርጋሉ ብዬ አስባለሁ።

የውጪ ባንኮች መግባት ሌላው ጥቅም አለው ብየ የማስበው በተለይ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ ያላቸው ልምድ ከፍተኛ ነው። የባንክ ሥራ በፍጥነት ወደ ዲጂታል ሥርዓት እየተቀየረ ነው ስለዚህ ከቴክኖሎጂ ሽግግር አንጻር ብዙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ልናገኝ አንችላለን የሚል እምነት አለኝ።

በጎረቤት አገራት ስለሚንቀሳቀሱ ባንኮች ትንሽ ልናገር። እነዚህ ባንኮች ከኛ የሚበልጡበት አንድ ነገር አለ። ይኸውም በሚሰጡት አገልግሎቶች ላይ ሁልጊዜ ኢኖቬሽኖችን ያደርጋሉ። ይሄ ማለት ከእኛ የተሻለ የማርኬቲንግ ክህሎት እንዳዳብሩ የሚያሳይ ነው።

ሌላው መናገር የምፈለገው ነገር በዓለማችን ላይ ትላልቅ ዓለማቀፍ አጀንዳዎች አሉ። እነዚህ ግሎባል አጀንዳዎች ላይ በእውነት እንናገር ካልን በእኛ በኩል ድክመት አለ ብየ አስባለሁ። ለምሳሌ የዘላቂ ልማት ግቦችን እንውሰድ።

እነዚህ ባንኮች አጀንዳዎቻቸውን ከእነዚህ ዓለማቀፍ አጀንዳዎች ጋር አቀራርቦ የመሰራት ልምድ አላቸው። ሌላው የአገር ውስጥ ባንኮች ራስን በማስተዋወቅ እና በፕሮሞሽን ሥራ ላይ ብዙ ይቀረናል ባይ ነኝ።

አሁን በአገራችን በቅርቡ የካፒታል ገበያ ተጀምሯል። በዚህ ገበያ ላይ ከእኛ ባንኮች በተሻለ የመጫወት ልምድ አላቸው። ነገርግን የውጪ ባንኮች ስጋት ብቻ ሳይሆኑ በተለይ በካፒታል ገበያ ላይ ጥሩ ልምድ የምናገኝባቸው ሊሆኑ ይችላሉ ብየ አስባለሁ።

ስፔሻላይዝድ የሆኑ ባንኮች ከመጡ ለምሳሴ በአነስተኛ እና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች ላይ የሚሰሩ ባንኮች ከመጡ ዘርፉን በተሻለ ያንቀሳቅሳሉ የሚል ሃሳብ አለኝ።

ሥጋት ተብሎ የሚታሰበው ዋናው ነገር እነዚህ ባንኮች ሲገቡ እንዴት እንቆጣጠራቸው የሚለው ነው። አርሱን ብሔራዊ ባንከ ሊያስብበት ይገባል። ባንኮቹ አሰራራቸው ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ፤አለመሆኑን ብ/ባንክ መቆጣጠር አለበት ማለቴ ነው ።

አንዴ ገበያውን ከከፈትን በኋላ አሰራራቸውን መቆጣጠር አለብን አንጂ አንዳይሰሩ ማለት ተፅዕኖ ማድረግ አይደለም።

በአጠቃላይ ይህ የመንግሥት ፖሊሲ እርምጃ በባንኮች መካከል ጠንካራ ውድድር እንዲኖር ያደርጋል። ለማጠቃለል ያህል

1ኛ/ ብሔራዊ ባንኩ ራሱን ከወዲሁ መዘጋጀት አለበት።

ማለት የውጪ ባንኮች መግባት ሳቢያ ሊኪሰት ከሚችል አደጋ አገርን መጠበቅ አለበት። ስለዚህ ራሱን ከወዲሁ ማዘጋጀት አለበት።

2ኛ/ መንግሥት ያስቀመጠው ፖሊሰ አንደሚለው የባንኮቹ የአገባብ መላዎች አንዱ በሳብሲደሪ ሲሆን ሌላው በሽርክና /ፓርትነርሺፕ ነው።

በበኩሌ ከሁለቱ ፓርትነርሺፕ ቅድሚያ ቢሰጠው ጥሩ ነው እላለሁ። ምክንያቱን ፓርትነርሺፕ ለአገር ውስጥ ባንኮች ከ70/30 ውስጥ የ70 በመቶ ባለድርሻ አንዲሆኑ እና የታሰበውን የዕውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት የተሻለ ዕድል ይኖረዋል።

ሳብሲዲየሪ የተባለው ዕድል ለውጪ ባንኮች የመቶ በመቶ መብት ስለሚሰጣቸው የአገር በቀል ባንኮች ይዋጣሉ የሚል ሥጋት አለ።

3ኛ/ የፋይናንስ ገበያው 5በመቶ ባንክ ላልሆኑ 30 በመቶ ደግሞ ለባንኮች መከፈትን አስመልክቶ እኛ ባንኮች አሰራሮችን እና ሌሎች ነገሮችን በጥንቃቄ ማሰብ አለብን ።

ስለዚህ አገር በቀል ባንኮች ቁጭ ብለው በጋራ ማሰብ ፤መወያየት፤ነገሮችን በጥንቃቄ ማየት አለብን ። የባንኮች የቦርድ አባላት እና አመራሮችም ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ብዬ አስባለሁ።

# “መንግስት የግሉ ዘርፍ በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ እድሉን ማመቻቸት አለበት” የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች ጥሪ

**በአሸናፊ ምትኩ**

በአንድ ሀገር ውስጥ የሰላምና ጸጥታ መስፈን ከበርካታ ጉዳዮች ጋር አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ትስስር እንዳለው እሙን ነው። የሰላምና ጸጥታ መረጋገጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማህበራዊ ፤ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮችን በመወሰን የላቀ ድርሻ እንዳለው ይታመናል። ዜጎች በሰላም ወጥተው ሰርተውና ምርታማ መሆን የሚችሉት አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ሲሰፍን እንደሆነ እሙን ነው። ተማሪው በአግባቡ እውቀት ቀስሞ ለሀገር ግንባታ አስተዋጾ ማድረግ የሚችለው ሰላምና ጸጥታ ሲኖር ብቻ ነው። ሰራተኛው በስራው ውጤታማና ምርታማ መሆን የሚችለው አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ሲሰፍን ነው ። በተለይም የአንድ ሀገር ሰላምና ጸጥታ ከአንድ ሀገር ምጣኔሀብታዊ እድገት እንዲሁም ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። የንግዱ ማህበረሰብ የተመረተውን ምርት መሸጥ የሚችለው የተረጋጋ ሀገርና ኢኮኖሚ ሲኖር ብቻ ነው ከዛ ውጪ ግን ህገወጥነት በህግ የበላይነት ይዋጥና አምራቹም ማምረት አይችልም ያልተመረተው ደግሞ ለገበያ ሊቀርብ አይችልም። የዚህ ድምር ውጤት የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ብሎም ፖቲካዊ አለመረጋጋትን እንደሚያስከትል የበርካታ ሀገራት ተሞክሮ ያሳያል። በአጠቃላይ የሰላምና ጸጥታ አለመኖር በአንድ ሀገር ላይ ሊያስከትል የሚችለው የኢኮኖሚም ሆነ ፖለቲካዊ ውጥንቅጥ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ የአለም ተሞክሮ ያሳያል። በኢትዮጵያም ከቅርብ አመታት ወዲህ በፖለቲካ አለመረጋጋትና በሰላም እጦት የተነሳ የዜጎች ህይወትና ንብረት በከንቱ ከመፍሰስ ባለፈ በምጣኔሀብት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው። አሁን ላይ በስፋት የሚስተዋሉ ፖለቲካዊ ችግሮች ጉዳታቸው እያንዳንዱን ዜጋ ለጉዳት የሚዳርጉ እንደመሆናቸው መጠን መፍትሄውም

ወደ ገጽ 10 ዞሯል > >>

# የግንባታው ኢንዱስትሪ ፈተናዎችና እድሎች...

ኢትዮጵያ በህዝቦቿ ቁጥር በአፍሪቃ አህጉር ከናይጄሪያ ቀጥላ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ከ110 ሚሊዮን ህዝብ በላይ እንዳላት የሚነገርላት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔ ከሚታይባቸው የአለማችን ሀገራት ተርታ ትመደባለች። ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የከተሜነት መስፋፋት እንደ መኖርያ ቤት የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን፤የስራ እድልን እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማዳረስ ትልቅ ፈተና እንደሆነ በዚህ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች ሲናገሩ ይደመጣል።

በቅርብ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ የከተሜነት እድገት በአመት በ4.7 በመቶ እያደገ እንደሆነ እና 21 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ደግሞ በከተማ የሚኖር ሲሆን ይህ አሀዝ በአፍሪቃ ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገራት የከተሜነት መጠን ጋር ሲነጻጸር የሀያ በመቶ ቅናሽ ያሳያል። እንደ መዲናይቱ አዲስ አበባ የመሳሰሉ ከተሞችን ስንመለከት ደግሞ የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣበት እና እንደ መኖርያ ቤት መንገድ እና ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ለማዳረስ ትልቅ ፈተና የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህ በዋናነት እንደ ምክንያት የሚቆጠረው ለግንባታ ግብአት የሚውሉ እንደ ብረት እና ሲሚንቶ የመሳሰሉ ምርቶች ዋጋ እና አቅርቦት ከፍላጎት ጋር አለመመጣጠን ፤በየወቅቱ እየናረ የመጣው የግንባታ ግብአት ዋጋ እና ደረጃቸውን ወይም ጥራታቸውን የጠበቁ የግንባታ ግብአቶች በቀላሉ አለማግኘት እንደሆነ በቅርብ የወጡ መረጃዎች ያሳያሉ።

በኢትዮጵያ የሚስተዋለውን የግንባታ ፍላጎትና አቅርቦት እንዲጣጣም ብሎም ጠንካራ የሆነ የግንባታ ኢንዱስትሪ እውን እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱ ተቋማት አንዱና ዋናው የኢትዮያ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ማህበር ይገኝበታል። ማህበሩ በቅርቡ በርካታ ባለድርሻ አካላትን በአንድ ላይ ያገናኘ የውይይት መድረክ አካሂዷል። የግንባታው ኢንዱስትሪ አሁናዊ እና መጻኢ እድል ላይ ርእሱን ባደረገው በዚህ የውይይት መድረክ ላይ በግንባታው ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ ባለሙዎች እና የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የግንባታው ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ ለአጠቃላይ ምርት እድገትም ሆነ ለስራ እድል ፈጠራ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም የግብአት አቅርቦት እና ፍላጎት ክፍተት መኖሩን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር መስፍን ነገዎ ሀሳባቸውን አካፍለዋል። ከዚህም ባለፈ ያለውን ግብአት በአግባቡ ያለመጠቀም ችግር እንደ ብረት በመሳሰሉ ምርቶች ላይ ብክነት በስፋት እንደሚስተዋል አክለው ተናግረዋል።

ሁለቱ የግንባታ ግብአቶች የሆኑት ብረትና ሲሚንቶ ለግንባታ ኢንዱስትሪው በተፈለገው መጠንና ጥራት አለመገኘት ራስ ምታት ሆነው ቀጥለዋል። የብረት አቅርቦት ችግር በሚስተዋልባት ኢትዮጵያ የብረት አጠቃቀም አያያዝ ችግር በግንባታ ሂደት ውስጥ እንደሚስተዋል መረጃዎች ያሳያሉ። ለአብነትም ያክል አብዛኛው በኢትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክቶች እስከ 35 በመቶ የብረት ብክለት እንደሚታይባቸው ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህም ባለፈ እንደ ብረት የመሳሰሉ የግንባታ ግብአቶች በበርካታ የውጭ ምንዛሬ ወጪ ተደርጎባቸው ከውጭ ሀገር የሚገቡ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ የገበያ ችግር እንደሚስተዋልበት የዘርፉ ከፍተኛ አማካሪ የሆኑት ዶ/ር ሙሉጌታ ገ/መድህን ተናግረዋል። ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው የብረት ጥራት አጠያያቂ እንደሆነ እና ችግር እንዳለበት ተናግረዋል። ከዚህም ባለፈ ህገ ወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ የብረት ገበያን ከሚፈታተኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደሆነ ዶ/ር ሙሉጌታ ተናግረዋል። በዚህም የተነሳ ታዲያ በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ እንደሆነ አክለው ገልጸዋል። ዘርፉን ከሚያጋጥሙት ችግሮች መካከል በህጋዊ ሰነድ አለመስራት ወይም ( illicit trade) እና የዋጋ መዋዠቅ ከፍተኛ መሆን እንደ አንድ ተግዳሮት እንደሚነሳ ገለጽዋል። ለአብነትም ያክል በባለፉት ሁለት አመታት የነበረውን የብረት ዋጋ ዝርዝር ሲታይ ዋጋው ፍጹም ያልተረጋጋ መሆኑን ደ/ር ሙሉጌታ የገለጹ ሲሆን ይህ የብረት ዋጋን ለመተንበይ እና የፕሮጀክት ወጪን ለማወቅ አስቸጋሪ እንደሆነ ተናግረዋል። የግንባታ ኢንዱስትሪው ሌላው ፈተና የውጭ ምንዛሬ እጥረት መሆኑን የገለጹት የዘርፉ ከፍተኛ አማካሪ የብረት ቁርጥራጮችን ከውጭ ሀገር የሚያስገባ አስመጪ ባለመኖሩ የሀገር ውስጥ የብረት ምርት እንደልብ እንዳይገኝ አድርጎታል ብለዋል።



ምስል፡ በግንባታ ኢንዱስትሪ ላይ የተደረገ የውይይት መድረክ

በብረት ጥራት ላይ የሚደረጉ የማጭበርበር ድርጊቶች በግንባታ አልሚዎችና በደንበኞች መካከል ከፍተኛ የሆነ ውዝግብ እያስነሱ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ማህበር ፕረዚደንት ኢንጂነር ግርማ ናቸው። ከውጭ ሀገር የሚገቡ ብረቶች ዋጋ ከፍተኛ መሆን ፤ የብረት ማስረከብ ሂደት ረዘም ያለ ጊዜን መውሰዱ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በማስተጓጎል የግንባታው ኢንዱስትሪ ፈተናዎች ናቸው ብለዋል ኢንጂነር ግርማ።

በብረት ላይ የሚደረስ ብክለትን ለመከላከል ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን መቅሰምና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ቁሳቁሶችን መልሶ የመጠቀም ባህል መዳበር እንዳለበት በግንባታው ኢንዱስትሪ ረጅም ልምድ ያካበቱት ባለሙዎች የሚናገሩት።

የግንባታው ኢንዱስትሪ የሰው ልጅ መጠለያዎች አልያም የስራ ቦታዎች እንደመሆናቸው መጠን የምንጠቀማቸው ግብአቶች ጥራታቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው ያሉት ደግሞ የየኛ ትሬዲንግ ዋና ስራ አስፈጻሚ ኦፊሰር ተመስገን አለማየሁ ናቸው። እኛ ትፍር ለማግኘት ብለን የሰው ልጅ ሂወትን አደጋ ላይ መጣል የለብንም ያሉት እኚህ አስተያየት ሰጪ ንግድ በዘላቂነት እንዲቀጥል ከትርፍ ይልቅ የደንበኞችን ፍላጎት ማርካታ ትልቅ ቦታ አለው ብለዋል። በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ቤት የሚገባውን የግንባታ ብረት መንግስት ትኩረት ሰጥቶት ሊከታተለው ይገባል ብለዋል የዘርፉ ባለሙያዎች። ከዚህም ባለፈ መንግስት የብረትም ሆነ የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ እንዲስፋፉ በማድረግ ትልቅ ሚና ሊጫወት ይገባዋል ብለዋል የዘርፉ ተዋንያን። ረጅም ዘመናት ያስቆጠረው የግንባታ ኢንዱትሪን ለማዘመን የሚያስችል የምርምር ስራዎችን መስራት ፤የግንባታው ኢንዱስትሪ ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ እንዲሆን የጥራት ማረጋገጫ መመዘኛዎችን ማዘጋጀትና በግንባታ ዙርያ ጠንካራ ፖሊሲዎችን በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ ሊያበረክት የሚችለውን ሚና ማሳደግ እንደሚገባ ምክረሀሳብ ቀርቧል።

## በሃላፊነት የሚከወን ቢዝነስ (RBC)...

ከደንበኞች የሚመጡ ቅሬታዎችን በአግባቡ ተቀብሎ በምርታችን ላይ ማሳተካከያ እንድናደርግ ይረዳናል። አር.ቢ.ሲ ለትላልቆቹ ብቻ የሚተው ሥራ አይደለም። ትናንሽ ድርጅቶች የRBC ፖሊሲ አውጥተው በሥራ ላይ ቢያውሉት ለራሳቸው ዕድገት እና ዘላቂነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ባይ ናቸው ።

### “አር.ቢ.ሲ ኩባንያዎቹን ከጽንገተኛ ኪሣራ እና መክሰም ይታደጋል”



አቶ መንግሥቱ ተፈራ( የሥራ አመራር አማካሪ)

በአር.ቢሲ መርሆች መሠረት ተቋሙ ዘላቂ ሆነ ማለት ጥቅሙ ለአገር እና ለወገን እድገት ነው።

ለኩባንያው ሠራተኞችም ጭምር የሚጠቅም እና የሚበጅ ነው። ስለዚህ አር.ቢ.ሲ ለኩባንያ አመራር በጣም ወሳኝ የሆነ ፤ ሃላፊነትን ለሁሉም ሠራተኛ በየደረጃው የሚሰጥ፤ ማለትም የድርጅቱን ባለቤት፤የድርጅቱን ሠራተኞች በየዘርፋቸው ሃላፊነትን ቆርሶ የሚሰጥ፤ከሥጋት እና ከፍራቻ የጸዳ፤ለሁሉም ሰው ምቹ የሆነ አና ጤነኛ የንግድ ከባቢን ለመፍጠር የሚረዳ ጥበብ አንደሆነ ከስልጠናው ተረድቻለሁ ብለዋል።

በተለይ ወደ ውጪ የምንልክ ነጋዴዎች ከሆንን ፤ ደንበኞቻችን አር.ቢ.ሲን እንደ ቅድመ ሁኔታ ያዩታል፡ ፡ የውጪ ኩባንያዎች ከሁሉ አስቀድመው በእኛ አገር ስላለው ላኪ በቂ መረጃ ይሰበስባሉ።

ያ ላኪ ኩባንያ መልካም ስም እንዳለው፤ በሕገወጥ ተግባር አለመሳተፉን ወዘተ በጠበቆቻቸው በኩል ያጣራሉ። ስለዚህ በእኛ በኩል አር.ቢ.ሲን እና ሌሎች ዓለማቀፍ መመዘኛዎችን አሟልተን ፤ራሳችንን ብቁ አድርገን መጠበቅ የኛ ድርሻ ነው።

ከዴኒሽ ኢንዱስትሪ ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ይኸው ስልጠና አዲስ ቻምበር አባል ኩባንያዎቹን የRBC የንግድ አመራር መርሆችን በየድርጅታቸው ተግባራዊ አንዲደርጉ፤ግልጽነት እና ተጠያቂነት የተላበሰ የሥራ አካባቢ አንዲፈጥሩ፤ በደንበኞቻቸው ዘንድ ያላቸውን ታማኝነት አንዲያጎለብቱ፤ ዓለማቀፍ ተወዳዳሪዎች አንዲሆኑ ጭምር ለማገዝ ታስቦ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

# የግሉን ዘርፍ በታዳሽ ኃይል ልማት በስፋት እንዲሳተፍ




**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

ዛሬ ዛሬ የዓለማችን አሳሳቢ እና አንኳር የመነጋገሪያ ጉዳዮች ከሆኑት መካከል አንዱ የከባቢ አየር ስጋት የዚህ አገር አልያም የዛኛው አገር ፈተና ሳይሆን አደጋው ሁሉንም ሳይለይ የሚጎበኝ በመሆኑ ነው።

ደራሽ ጎርፍ እና የውሃ ሙላት፤ድርቅ፤ርሃብ የመሳሉት ችግሮች ድግግሞሽ ከመቼውም ጊዜ በይበልጥ እየታየ ነው። ይህንን ዓለማፍ ቀውስ ለመቀነስ አገራት ሃብታቸውን፤ እወቀታቸውን፤ ቴክኖሎጂያቸውን እያፈሰሱ ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው።

በእርግጥ የዚህ ችግል መነሻው ከኢንዱስትሪ አብዮት መከሰት እና ተከተትሎ የመጣው ሃይድሮ ካርበን (ነዳጅ )በጥቅም ላይ መዋል አንደሆነ ተመራማሪዎች ይናገራሉ።
አገራችንም በዚህ አንጻር እኤአ በ2011 የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ አውጥታ በሥራ ላይ አውላለች።

በዚህ አንቅስቃሴ ላይ መንግሥት ከሚያደርጋቸው የአካባቢ ፤የአፈር እና የውሃ ጥበቃ ስራዎች በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ ደግሞ በታዳሽ ኃይል ምንጬ እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የበኩሉን ተሳትፎ እየደረገ ነው።

የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ጎላ ብሎ የሚታየው በገጠር የጸሐይ ሃይል ማመንጨት እና መሸጥ ፤በጸሀይ ብርሃን ፓኔሎችን በማቅረብ እና ተዛማጅ መለዋወጫዎች እና ግብዓቶችን በማቅረብ ነው።




ነገር ግን በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን በማስመጣት፤ወይም በከፊል አልያም በሙሉ በመገጣጠም ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ የጀመሩ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ አርበኛ ነጋዴዎች ብቅ ብቅ እያሉ ነው።

በአገራችን ከፍተኛ የፍላጎት እና የአቅርቦት አለመጣጣም ከሚስተዋልባቸው አገልግሎቶች አንዱ ትራንስፖርት ነው።

በየጊዜው እያሻቀበ የሚወጣውን የነዳች ዋጋ አብሮ የሚጨምረውን የታሪፍ ዋጋ ሌላው በተገልጋዩ/ተሳፋሪው ሕዝብ የሚደርስ ተጨማሪ ጫና ነው።

በነገራችን ላይ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አገራችን በየአመቱ ወደ 80 ቢሊየን ብር ለነዳጅ ታወጣለች። ወደ 800 ሺህ የሚጠጉ ተሽከርካሪዎች ደግሞ በየቀኑ ይመላለሱበታል። ከእነዚህም አብዛኞቹ ዕድሜቼው የገፉ እና ከፍተኛ በካይ ጭስ ወደ ከባቢ አየር የሚለቁ ናቸው።
መንግሥት የችግሩን ዓለማቀፋዊ እና አገራዊ ኪሣራ በመመልተከት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ በተለይ በታዳሽ ኃይል ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ አንዲሳተፍ የተለያዩ የማበረታቻ ፖሊሲዎችን በሥራ ላይ ማዋሉ መልካም እርምጃ ነው።

በኤሌክትሪክ የሚዘወሩ መኪኖች በአገራችን አጭር ታሪክ ያለው ቢሆንም ከመንግሥት ጥረት ጎን ለጎን የንግዱ ሕ/ሰብ የግሉ ዘርፍ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን ወደ አገር ቤት እያስገባ አሊያም በአገር ውስጥ እንዲገጣጠሙ ማድረግ የእለት ተለት ክንውን መሆኑን ማየት ከጀመርን ሰንበት ብለናል።

መንግስት በኤሌክትሪክ ኃይል የሚዘወሩ መኪናዎችን አስመልክቶ ያስቀመጠው ማበረታቻ ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎችን ለሚከፍቱ ባለሃብቶች አስፈላጊ መሣሪያዎችን ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ፤ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ተገጣጥመው በሚገቡት ላይ አስከ 15 በመቶ፤በከፊል ተገጣጥመው ለሚገቡ 5 በመቶ እና ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ለሚገጣጠሙ ሙሉ በሙሉ ከቀርጥ ነጻ እንዲሆኑ የሚፈቅድ ነው።

ይህም መንግሥት ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓት ላይ ካደረገው ማበረታቻ ጋር ያልተናነሰ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በሙያቸው መካኒካል መሐንዲስ የሆኑት እና የኮረንቲ ሞተርስ ሥራ አሰኪያጅ አቶ ሚካኤል አስረሳኸኝ አንደሚሉት በኤሌክሪክ የሚሽከረከሩ አውቶ ሞቢሎችን እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ላለፉት 5 አመታት ፋና ወጊ ሆነው ሲያቀርቡ ቀይተዋል።

አገራችን የትራስፖርት አዋጁ በራሱ ከተለመደው የቤንዚን እና የናፍጣ በስተቀር በታዳሽ ሃይል ለሚሰሩ ተሽከርካሪዎች የሚለው ነገር አለመኖሩ፤በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ከቤንዚን እና በናፍጣ ከሚሰሩት እኩል ቀረጥ እና ታክስ ተጥሎ ቆይቶ ከቅርብ አመታት ወዲህ መንግሥት የቀረጥ ማሻሻያ መድረጉን ያስታውሳሉ።



አቶ ሚካኤል እንደሚሉት በነዳጅ እና በናፍጣ ለሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ተብሎ ለነዳጅ፤ ለቅባት፤ ለመለዋወጫ፤ የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ ሙሉ በሙሉ የሚያሰቀሩት እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንደኛ ላሉ የዕዳ ጫና፤በፔትሮሊየም ጥገኝነት ሥር ላሉ አገራት እፎይታ ነው ይላሉ።

የአገራችን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ታሪክ ከአካባቢው አገራት ጋር ሲነጻጸር ርካሽ ነው። አንድ በቤንዚን የሚሰራ መኪና በአንድ ሊትር 12 ኪ/ሜ ይጓዛል አንበ።

ከአ/አ ወደ ደሴ ለመሄድ 400 ኪ/ሜትር ለመጓዝ ወደ 33 ሊትር ቤንዚን በ60 ብር ሂሣብ ቢገዛ ወደ 2000 ብር ወጪ ያደርጋል። ነገር ግን አንድ በ70 ብር በኤሌክትሪክ የተሞላ መኪና ይህንኑ 400 ኪሎ ለመጓዝ ያስችላል።

ድሮ ድሮ እንዳዛሬው የእንጀራ መጋገሪያ የኢሌክትሪክ ምጣድ በየመንደሩ መፈብረክ ሳይጀመር ሕብረተሰቡ በቶሎ እነዳልተቀበለው ይታወሳል።

ሕብረተሰባችን ወደ አማራጬ የኃይል ምንጬ አጠቃቀም የሚደርገው ሽግግር “ለማያውቁት መልአክ...” አይነት ጊዜ የወሰደ በፈጣን ሁኔታ ሳይሆን በአገራችን ሰፊ ፍላጎት አንዳለ ከቀን ወደ ቀን በየጎዳናው ላይ የሚሽከረከሩት መኪናዎች ቁጥር ጥሩ ማሳያ ነው።

ነገር ግን በአገራችን ያለውን የታዳሽ ሃይል እምቅ ኢንቨስትመንት ዕድሎችን እና አማራጬች ላይ መንግሥት እና የንግዱ ሕብረተሰብ ሰፊ የፕሮሞሽን ሥራዎችን በትብብር መሥራት አንዳለባቸው ለመጠቆም አንወዳለን።

# ለግምገማ ከገቡት የሂሳብ መግለጫዎች ውስጥ ትኩረት የሚፈልጉ ክፍተቶች መገኘታቸው ተገለጸ።

**በሠናይት እሸቱ**

በአለም አቀፍ ደረጃ በ167 ሃገሮች እየተተገበረ የሚገኘው የአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ በሃገራችን ጥቂት የማይባሉ ድርጅቶች ተግባር ላይ ቢያውሉትም በቂ እውቀት ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ክፍተቶች መታየታቸው ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር ቦርዱ ከተደራጀ እና ወደስራ ከገባ ጀምሮ በገቡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ የታዩ ችግሮች ምን ነበሩ መፍትሄዎቻቸውስ በሚለው ላይ ያተኮረ ስልጠና አካሂዷል።
በስልጠናው ከመቶ በላይ የድርጅት የሂሳብ ባለሞያዎች እና ባለቤቶች ተሳትፈውበታል።
የኦዲት ቦርዱ የኦዲት ሪፖርቶችን መገምገም ከጀመረ አመት የሆነው ሲሆን፡ ለግምገማ የቀረበው ሪፖርት የአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃን ተረድቶ የተሰራ እንደማይመስል የኦዲት ቦርዱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ሂክመት አብደላ ስልጠናውን ሲያስጀምሩ ተናግረዋል።
40 የሚደርሱ ድርጅቶች የኦዲት ግምገማ ግኝት በቀረበበት በዚሁ ስልጠና ላይ ማብራርያ የሰጡት የኦዲት ቦርዱ አማካሪ አቶ ደረጀ ገላና ፡ ግኝቶቹ በአራት ደረጃ ተከፋፍለው የተቀመጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል ከነዚህም ውስጥ ሪፖርቱ ከ IFRS ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ በድጋሚ እንዲሰራ የሚመለስ፡ ወደፊት ሊስተካከል የሚችል በሚል እንደ ግኙቱ ደረጃ የተቀመጠ መሆኑን አንስተዋል።
አማካሪው አክለውም ምንም እንኳ የኦዲት ግምገማዎቹ ትላልቅ እና ስራ የሚፈልጉ ግኝቶች ያሉት ቢሆንም በተደጋጋሚ በማሰልጠን እና አቅምን በማሳደግ መሻሻል ሊመጣ እንደሚችል አንስተዋል።
አሰራሩን ተግባራዊ ያላደረጉት ድርጅቶች መሰል ስልጠናዎች ማግኘታቸው የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ የሚያግዝ መሆኑንም ገልጸዋል።
የኦዲት ግኝቶቹ ከእውቀት ክፍተት የተከሰቱ መሆናቸውን የገለጹት አማካሪው ከዚህ ቀደም ስራ ላይ ይውል የነበረው አሰራር ተጽኖ የፈጠረ መሆኑን እና IFRS አሰራር በትምህርት ስርአቱ ተካቶ ተምረው የሚወጡት የተሻለ የመተግበር አቅም ይኖራቸዋል ብለዋል።
እዚህ ደረጃ እስከሚደረስም ድርጅቶች በአማካሪነት አብረዋቸው የሚሰሩትን አማካሪዎች ሪፖርቱ ተገምግሞ ውጤቱ እስከሚታውቅ አብረዋቸው እንዲቆዩ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።